አፍሪካ ቲቪ

4

# አፍሪካ አካዳሚ

AFRICA ACADEMY

www.AfricaAcademy.com

# ሁሉም ሙስሊም ማወቅ ያለበት አዝካር ፣ ዱዓዕ እና ከፍተኛ ምንዳ ያላቸው ሥራዎች 5

በቴሌግራም

AAcademyEthio

www.AfricaAcademy.com

...ማሳሰቢያዎች፡-

(5) በህብረት ማንበብ ከሱና ጋር ይፃረራል፡፡ ስለዚህ የተዘገበው ሐዲስ ደካማ ነው፡፡ እንደዚሁም በካሴት ንባብ ብቻ መብቃቃት አይገባም፡፡ ምክንቱም ሩቅያ የሚያደርግ ሰው ሊያሟላው ከሚገቡ ነገሮች አንዱ ኒያ ነው፡፡ ይህ ደግሞ በካሴት አይቻልም፡፡ ሆኖም መስማቱ ጠቀሜታ አለው፡፡ በጣም የሚያታክት ካልሆነ በስተቀር እስከሚድን ድረስ መደጋገሙ ይወደዳል፡፡ አንቀፆችን በተወሰነ ቁጥር መደጋገም (ይህን ያህል ጊዜ ነው) የሚገባው ማለት በመረጃ ካልሆነ ተቀባይነት የለውም፡፡

(6) ሩቅያ አድራጊው በቁርአን ሳይሆን በድግምት እየተጠቀመ መሆኑን የሚያመላክቱ መረጃዎች አሉ፡፡ አንዳንድ ሰዎች ሀይማኖተኛ መስለው በመቅረቡ ሊያሞኙን አይገባም፡፡ አንዳንድ ሰው በቁርአን ይጀምርና ወዲያውኑ ወደ ሌላ ሊቀይር ይችላል፡፡ ሰዎችን ለማሞኘት መስጂድን የሚያዘወትር ሊሆንም ይችላል፡፡
ሰው ፊት አላህን በብዛት የሚዘክር (የሚያወሳም)
ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ እንዳያሞኝህ፡፡



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

## ከመተተኞች ድግምተኞች አስማተኞችና አባይ ጠንቋዮች ምልክቶች መካከል ከዚህ በታች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የበሽተኛውን ስም ወይም የእናቱን ስም መጠየቅ፡፡ ስምን ማወቅና አለማወቅ ከህክምናው ጋር ምንም ግንኙነት የሌለው መሆኑ እየታወቀ
- የበሽተኛውን ልብሶችን ከናቲራና ከውስጥ የሚለበሱ ልብሶች የመሳሰሉትን አምጡ ብሎ መጠየቅ፤
- እንዲህ እንዲያ ዓይነት መልክ ያላትን እንስሳ ለጅን እረዱ ማለት ከዚያም አልፎ ከደሙም በሽተኛው እንዲቀባ ማዘዝ፤
- ምንም ትርጉም የሌላቸውን ቃላት መፃፍ ወይም ማንበብ፤

4

- አራት ረድፍ (ሰንጠዥ ያለባቸው) የታጠፉ ወረቀቶችን ፅፎ እንዲያንጠለጥል ማዘዝ፤
- በሽተኛው ከሰው ተነጥሎ ለብቻው በጨለማ ቤት እንዲያሳልፍ ማድረግ፤
- ለተወሰነ ጊዜ ውሃ እንዳይነካ ማዘዝ፤
- በሽተኛው የሚቀብረው ነገር ወይም አቃጥሎ የሚሞቀው ወረቀት መስጠት፤
- በሽተኛው ሳይናገር አስቀድሞ መናገር፤
- ስለ በሽተኛው ሁኔታ ገና ሲገባ ወይም በስልክ ወይም በፖስታ መናገርና የመሣሠሉት ናቸው፡፡

(7) የሱና ተከታዮች ጂኖች በሰው መመሰል እንደሚችሉ ነው የሚያምኑት፡፡

መረጃውም አላህ (እነዚያ አራጣን (ሪባን) የሚበሉ ያ በሰይጣን በመነካቱ የተነሳ ሰይጣን የሚጥለው ሰው (ከውድቀቱ) እንደሚነሳ ቢጤ እንጂ (ከመቃብራቸው) አይነሱም፡፡) የሚለው ነው፡፡

- በሁሉም የቁርአን አብራሪዎች (ሙፈሲሮች) ስምምነት መሰረት ይህ አባባል በሰይጣን መጠናወት ምክንያት የሚፈጠር እብደት ነው ብለዋል፡፡

## ማጠቃለያ፡-

- ሲህር (ድግምት) መኖሩ የታወቀ ነው፡፡
- በሰዎች ላይ ተፅኖ ማሳደሩ በቁርአንም ሆነ በሐዲስ የተረጋገጠ ነው፡፡
- ድግምት ክልክል ነው፡፡ ትልቅ ወንጀልም ነው፡፡
- ምክንያቱም ነቢዩ ሰ.ዐ.ወ ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ:- (ሰባት አደገኛ አጥፊ የሰውን ልጅ ጎጂ የሆነ ወንጀሎችን ተጠንቀቁ ብለው ሲያስተምሩ ምን ምን ናቸው? ሲሏቸው:- (በአላህ ማጋራት፤ ሲህር (ድግምት)...) ብለዋልና ነው፡፡
- አላህም፡- “በመጨረሻይቱ አገር ምንም ዕድል የሌለው መሆኑን በእርግጥ ተገንዝበዋል፡፡በአላህ መለኮታዊ መልዕክት እና መመሪያ ምትክ ድግምትን በመለወጥ ነፍሶቻቸውን የሸጡበት ነገር ምንኛ ከፋ። ..የሚጠቅማቸውን የሚያውቁ ቢሆኑ ኖሮ ወደዚህ አሳፋሪ ተግባር እና ግልፅ ጥምመት ባልገቡ ነበር።” ብሏል፡፡

4

- **ድግምት ለሁለት ይከፈላል፡፡**

1) በወረቀት የሚተበተብና ድግምተኛው ሰይጣንን እንደፈለገ ለመጠቀም የሚችልበት ነው፡፡

2) ድግምት የተደረገበትን ሰው አካል፤ አዕምሮ፤ ፍላጎትና ስሜት ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድር መድሀኒት ነው፡፡ ከዚያም የተደገመበት ሰው ጎዳዩ የተቀየረ ይመስለዋል፡፡ የቆመው የሚሄድ፤ ነገሩ ሁሉ በተገላቢጦሽ ይታየዋል፡፡ ይህም ክፍል መስተፋቅር ይባላል፡፡

- የመጀመሪያውን ክፍል መተግበር ከኢስላም የሚያወጣ ክህደት ነው፡፡ ምክንያቱም ሰይጣናት ለዚህ አገልግሎት የሚተባበሩ በአላህ መካዱን ሲያረጋግጡ ብቻ ነውና፡፡ ሁለተኛውን መስራት ግን ከታላላቅ ወንጀሎች አንዱ ነው፡፡ ሁሉም የሚሆነው በአላህ ውሳኔ ብቻ ነው፡፡